Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 1-0/425/08
Ref. No
ቀን 25 ህዳር 2008
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡ የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣት እና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 112/2008 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ ስለሆነ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ።።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፤

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- ለኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይን ልማት ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለቅርንጫ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለህግ ጥናት፣ ረቂቅና ዝግጅት ስልጠና ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

28/03/08
ሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣት እና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ

## ቁጥር 112/2008

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ጥቅምት 2008
አዲስ አበባ

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



# የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣት እና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ

## ቁጥር 112/2008

ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣምና በሀገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እንዲሁም ሕጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ዘመናዊ የጉምሩክ ሕግ ማዕቀፍ ጸድቆ ስራ ላይ የዋለ በመሆኑ፣

ከአዲሱ ጉምሩክ ህግ ጋር የተጣጣመ ከጉምሩክ አሠራር ጋር የሚፈጸሙ ጥፋቶች በአስተዳደራዊ ቅጣት የሚስተናገዱበት አግባብ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ መመሪያ በማስፈለጉ፣

ዕቃዎችና ማጓጓዣዎችን ስለመያዝ፣ ስለማጣራት ስለመውረስና ስለውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት አንድ ወጥ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ ባለሥልጣኑ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 148/1/ እና አንቀጽ 180/2/ እና በባለስልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 6/19፤20/2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል 1

### ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣት እና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 112/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

1/ "አስተዳደራዊ ውሳኔ" ማለት የጉምሩክ ስራን በኃላፊነት እንዲያከናውን በተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ወይም ኮሚቴ ወይም ክፍል በጉምሩክ ስራ በአስተዳደራዊ መንገድ በሚታዩ የጉምሩክ ጥፋቶች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ሲሆን በባለስልጣኑ አቃብያነ ህግ የሚሰጡ ውሳኔዎችን አይጨምርም፤

2/ "አቤቱታ" ማለት በአስተዳደራዊ ውሳኔ፣ በአስተዳደራዊ መቀጫ ወይም በዕቃዎችና በማጓጓዣዎች ላይ በሚሰጥ የመያዝ ወይም ውርስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ነው፤

3/ "አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል" ማለት በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተቋቋመ የጉምሩክ ጉዳዮችን አቤቱታ አይቶ የሚወስን ክፍል ነው፤

4/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፤

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

5/ "መውረስ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 147 ላይ የተገለጹትን ዕቃዎች ወይም ማጓጓዣዎች ለመንግስት ገቢ ማድረግ ነው፤

6/ በዚህ መመሪያ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ ክፍል ሰባት ምዕራፍ አንድ ላይ በተደነገጉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች አፈፃፀም እና በአዋጁ መሰረት በሚወረሱ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጥፋቶች አይነትና የቅጣት እርምጃዎች

4. <u>በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የተጣለ ገደብን አለማክበር</u>

1/ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀፅ 156 /1/ መሠረት ገደብ የተደረገበትን ዕቃ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ወይም ከሀገር ያስወጣ ወይም ለማስወጣት የሞከረ እንደሆነና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃድ ማቅረብ ካልቻለ፣

ሀ) ድርጊቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ ብር 10,000 /ብር አስር ሺ/፣

ለ) ድርጊቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ ብር 25,000 /ብር ሃያ አምስት ሺ/፣ወይም

ሐ) ድርጊቱ ለሦስተኛ ጊዜ እና በላይ የተፈፀመ ከሆነ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺ ብር/ መቀጮ ይቀጣል፣

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ለማቅረብ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ በአንድ ወር ውስጥ በአስመጭው አማካኝነት ተመልሶ እንዲወጣ፣ የወጪ ዕቃ ከሆነም ከሀገር እንዳይወጣ ይደረጋል፤

3/ ማንኛውም መንገደኛ ይዞት የተገኘ ዕቃ በብዛት ወይም በዋጋ በህግ ወይም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃውን ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



5. <u>ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል ወይም አንሶ እንዲከፈል ስለማድረግ</u>

1/ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 157(1) መሰረት ለጉምሩክ ፎርማሊቲ በቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወይም አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም ከሀገር እንዲወጣ ካደረገ ወይም ከሀገር እንዲወጣ ለማድረግ የሞከረ እንደሆነ ያልተከፈለው የዕቃው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚሁ ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

2/ በዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት የወጪ፣ ዕቃ በሚሆንበት ጊዜና ዕቃው በሰነዱ ላይ ከተገለጸው ብልጫ ያለው ሆኖ ሲገኝ ዕቃው እንደ ገቢ ዕቃ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን ቅጣት በመክፈል ዕቃው ሳይያዝ ልዩነቱ ተመዝግቦ ሰነዱ በዕቃው መጠን እንዲስተካከል ይደረጋል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በጠቅላላ ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ በብልጫ ከሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ከ10% /አስር በመቶ/ የማይበልጥ ከሆነ አስመጪው በልዩነት የተገኘውን ቀረጥና ታክስ ያለ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፣

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) ድንጋጌ ቢኖርም ተደብቆ የተገኘው ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለጸው ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ 50% በላይ የሆነ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 169/2/ መሰረት ምርመራ እንዲጣራበት ለወንጀል ምርመራ ቡድን ሰነዱ መላክ ይኖርበታል።

5/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 አፈጻጸም "ተደብቆ የተገኘ ዕቃ" ማለት ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ወይም ያልተመዘገበ ዕቃ ማለት ነው።

6/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም "ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ" ማለት በዲክላራሲዮኑ ላይ ከተሰጠው መግለጫ ጋር ሲነጻጸር በመጠን፣ በዓይነት፣ በስሪት ሀገር፣ በምርት ዘመን ፣ የቀረጥና ታክስ ልዩነት የተገኘበት ዕቃ ማለት ነው፣

7/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም "ያልተመዘገበ ዕቃ" ማለት በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበው ዕቃ በዓይነት ወይም በብዛት የተለየ ዕቃ ማለት ነው።

8/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 3 እና 4 ድንጋጌዎች በቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ለኢንቨስትመንት ስራ ወይም ለሌላ ለማንኛውም አገልግሎት በቀረጥ ነጻ በሚገቡ ዕቃዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፣

6. <u>እሽጎችን ስለመፍታትና ምልክቶችን ስለማንሳት</u>

1/ ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በማጓጓዣ ወይም በኮንቴይነር ላይ የተደረገውን የጉምሩክ ማሸጊያ የፈታ፣ ያላቀቀ፣ ዕቃ ወይም የዕቃው ማያዣ ላይ የተደረገውን ምልክት ያነሳ፣ የፋቀ፣ የሰረዘ ወይም የለወጠ ወይም የዕቃን መያዣ የከፈተ ወይም ጥቅሎቹን የበተነ እንደሆነ፣

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ሀ) ድርጊቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 10,000 /ብር አስር ሺ/፣

ለ) ድርጊቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ እንደሆነ ብር 25,000 /ብር ሃያ አምስት ሺ/፣ ወይም

ሐ) ድርጊቱ ለሦስተኛ ጊዜ እና/ወይም በላይ ወይም ተደራርቦ የተፈፀመ ሲሆን ብር 50,000 /ሃምሣ ሺ ብር/ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸም ላይ በቀጥታ ተጽዕኖ የሚያመጣ አደጋ ወይም በጉዞ ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ድርጊቱን አቅራቢያው ለሚገኝ የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት፣ ጣቢያ ወይም የህግ አስከባሪ አካል ቀድሞ ያሳወቀ ከሆነ እና ለዚሁም ማስረጃ ያቀረበ እንደሆነ ቅጣቱ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

7. <u>ናሙናዎችን አለመመለስ</u>

1/ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀፅ 159 መሠረት ለናሙና የወሰደውን ዕቃ ያልመለሰ ወይም በዕቃው የተገለገለ ወይም ዕቃው እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ የዕቃውን ዋጋ፣ ቀረጡንና ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ በአዋጁ አንቀጽ 55(2) መሰረት ለናሙና የተወሰደው ዕቃ ያልተመለሰበት ምክንያት በተፈጥሯቸው በምርመራ ሂደት የሚባከኑ ወይም ለማነጻጸሪያ የሚፈለጉ በመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ዓላማ ናሙናው እንደተመለሰ ይቆጠራል፡፡

8. <u>የአጓጓዥ ግዴታዎችን ያለማክበር</u>

ማንኛውም አጓጓዥ፡-

1/ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተሟላ የመንገደኞች ወይም የጭነት መግለጫ ለመጀመሪያ ጊዜ ያላቀረበ ከሆነ ብር 3,000.00/ሦስት ሺ/ ለሁለተኛ ጊዜ ያላቀረበ ከሆነ ብር 4,000.00/አራት ሺ/ ለሦስተኛ ጊዜና በላይ ያላቀረበ ከሆነ ብር 5,000.00 /አምስት ሺ/ ፤

2/ ከተፈቀደለት ሰው ሌላ ወደ ማጓጓዣው እንዲገባ ያደረገው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ብር 2,000.00/ሁለት ሺ/ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን ብር 3,500.00 /ሦስት ሺ አምስት መቶ/ ለሦስተኛ ጊዜና ከዚያ በላይ ሲሆን ብር 5,000.00 /አምስት ሺ/፤

3/ ማጓጓዣው ከጉምሩክ ወደብ እንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ከጉምሩክ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ ከ12 ሰዓት በላይ ከወደብ ሳይወጣ የዘገየ እንደሆነ ድርጊቱ የተፈጸመው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ብር 2,500.00/ሁለት ሺ አምስት መቶ/ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ብር 4,000.00/አራት ሺ/ ለሦስተኛ ጊዜና በላይ ከሆነ ብር 5,000.00/አምስት ሺ/፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (2) (3) ውስጥ ከተመለከቱት ጥፋቶች ሁለቱን በአንድ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጽሞ ሲገኝ ብር 3,500.00/ሦስት ሺ አምስት መቶ/ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን ብር 4,000.00/አራት ሺ/ ለሦስተኛና ከዚያ በላይ ሲሆን ብር 5,000.00/አምስት ሺ/፤

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (2) (3) ላይ የተጠቀሱትን ሦስቱንም ጥፋቶች በአንድ ላይ በተደራራቢነት አጣምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጽሞ ሲገኝ ብር 4,000.00/አራት ሺ/ ለሁለተኛ ጊዜና ከዚያ በላይ ሲሆን ብር 5,000.00/አምስት ሺ/፤

6/ ጉምሩክ ወደብ በደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ወይም ከጉምሩክ ሹም በግልጽ የተሰጠ ፈቃድ ሳያገኝ ዕቃ ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሙከራ ያደረገ እና ሙከራው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን ብር 7,000.00 /ሰባት ሺ/ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን 8,500.00 /ስምንት ሺ አምስት መቶ/ ለሦስተኛና ከዚያ በላይ ሲሆን ብር 10,000.00/አስር ሺ/፣

7/ ጉምሩክ ወደብ በደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ወይም ከጉምሩክ ሹም በግልጽ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር ዕቃ የጫነ ወይም ያራገፈ ከሆነ ድርጊቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን ብር 8,000.00/ስምንት ሺ/ ድርጊቱ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን ብር 9,000.00/ዘጠኝ ሺ/ ድርጊቱ ለሦስተኛ ጊዜና ከዚያ በላይ የተፈጸመ ሲሆን ብር 10,000.00 /አስር ሺ/ ይቀጣል፡፡

9. <u>የጉምሩክ መጋዘን ባለ ፈቃድ ግዴታዎችን አለማክበር</u>

1/ የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ ለጉምሩክ ስራ አስፈላጊ የሆኑ

ሀ) ቢሮዎችን፣ መሳሪያዎችን፣ ቴክኖሎጂዎችንና ሰራተኞችን ያላሟላ እንደሆነ ወይም፣

ለ) ወደ መጋዘኑ የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችን ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 56 ንዑስ 3/ሀ/ የተመለከተውን ለማስፈጸም በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ያልመዘገበና በየጊዜው ለባለስልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ወይም፣

ሐ) በመጋዘኑ የሚቀመጡትን ዕቃዎች እንደዓይነታቸውና እንደባህሪያቸው በመለየት ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ ያላስቀመጠ እንደሆነ ወይም፣

መ) የተሰጠውን የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በወቅቱ ያላሳደሰ እንደሆነ ወይም፤

ሠ) በአያያዝ ጉድለት የጠፋ ወይም የተበላሹ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ ያልከፈለ እንደሆነ፣ወይም

ረ) መጋዘኑ ጊዜያዊ የጉምሩክ ማከማቻ ሲሆን የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተከናወነበት ዕቃ በአዋጁ አንቀጽ 51(6) መሰረት ከመጋዘን እንዲወጣ ያላደረገ ከሆነ ወይም፣

ሰ) መጋዘኑ ጊዜያዊ የጉምሩክ ማከማቻ ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 51(7) መሰረት የተፈቀደው የጊዜ ገደብ ያለፈባቸውን በመጋዘን የተከማቹ ዕቃዎች ለባለስልጣኑ ያላሳወቀና ዕቃዎችን ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን ያላስተላለፈ ከሆነ፤

ከነዚህ አንዱን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ብር 50,000.00/ሀምሳ ሺ/ ብር ይቀጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ (1) ከሀ-ሰ ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ብር 70.000.00/ሰባ ሺህ/ ብር ይቀጣል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ግዴታዎች ውስጥ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑትን ጥፋቶች በጣምራ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጽሞ ሲገኝ ብር 75,000.00/ሰባ አምስት ሺ/ ብር ይቀጣል፤

4/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱን ለሦስተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸውን የጣምራ ጥፋት ለሁለተኛ እና በላይ ፈጽሞ ሲገኝ ብር 100,000.00/ አንድ መቶ ሺህ ብር/ ይቀጣል፡፡

5/ ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ፡-

ሀ) የጉምሩክ ሹም ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ያልሰጠ እንደሆነ ለቁጥጥርና ለምርመራ ስራ እንዲተባበር ተጠይቆ ያልተባበረ እንደሆነ ወይም፣

ለ) በባለስልጣኑ ያልተፈቀደ ዕቃ ወደ መጋዘን እንዳይገባ ወይም ከመጋዘን እንዳይወጣ መቆጣጠር ሲገባው ያልተቆጣጠር እንደሆነ ወይም፣

ሐ) ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ መጋዘን አስገብቶ የተገኘ እንደሆነ ወይም፣

መ) የጤና ምርመራ ሊደረግበት የሚገባ ዕቃ ከማጓጓዣው እንደተራገፈ አስፈላጊው የጤና ምርመራ እስከሚፈጸም ድረስ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይቶ በኳራንቲን ክልል እንዲቆይ ያላደረገ እንደሆነ ወይም፣

ሠ) ወደ መጋዘኑ መግባት ያለባቸው ዕቃዎች ያልገቡ እንደሆነና ያለመግባታቸውን ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ወይም፣

ረ) መጋዘኑ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ከሆነ ዕቃዎቹ ለተፈቀደላቸው አላማ ሳይውሉ ሲቀሩ ማስያዝ የሚገባውን ዋስትና ያልያሳዘ እንደሆነ፤

ብር 70,000.00/ሰባ ሺህ/ ይቀጣል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (5) የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በአንድ ላይ ፈጽሞ ሲገኝ ብር 100,000.00/አንድ መቶ ሺህ/ ይቀጣል፡፡

10. <u>የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ ሥርዓትን አለማክበር</u>

በአዋጁ አንቀጽ 162 ላይ የተገለጸውን የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ-ሥርዓትን በሚመለከት ተፈጻሚነት የሚኖረውን የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት ባለማክበር

1/ ማንኛውም አጓጓዥ

ሀ) በባለስልጣኑ ከተፈቀደ የጉዞ መስመር ውጪ ዕቃን ካጓጓዘ ወይም፣

ለ) ዕቃ ጭኖ እንዲንቀሳቀስ በተገደበለት ጊዜ አጓጓዞ ያላደረሰ እንደሆነ ወይም፣

ሐ) ገቢና ተላላፊ ዕቃዎችን በጉምሩክ ማሸጊያ ታሽገው መጓጓዝ የሚገባው ሆኖ ሳይታሸግ ሲያጓጉዝ የተገኘ እንደሆነ ወይም፣

መ) በጉምሩክ ከተፈቀደ የጉምሩክ መውጫና መግቢያ ውጪ ዕቃ ያስወጣ ወይም ያስገባ እንደሆነ፤

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ - መ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 5,000 /አምስት ሺ/፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ - መ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 10,000 /አስር ሺ/፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ - መ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ለሦስተኛ ጊዜ እና/ወይም ከዚህ በላይ የተፈፀመ ሲሆን ብር 20,000 /ሃያ ሺ/፣
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ -መ የተዘረዘሩት ድርጊቶች ተደራርበው ሲገኙ ብር 20,000/ ሃያ ሺ/ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ ማንኛውም ዲክላራሲዮን አቅራቢ እና /ወይም አጓጓዥ

ሀ) የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃዎች በባለስልጣኑ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ተከብረውና ደህንነታቸው ተጠብቆ መድረሳቸውን ያላሳወቀ እንደሆነ ወይም፣

ለ) የወጭ ዕቃ ወይም ከጉምሩክ ጣቢያ ወደ ጉምሩክ ጣቢያ ዕቃዎችን በጉምሩክ ማሸጊያ ታሽገው መጓጓዝ የሚገባቸው ሆኖ ሳያሳሽግ ሲያጓጉዝ የተገኘ፣

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ - መ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 5,000 /አምስት ሺ/፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ - መ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 10,000 /አስር ሺ/፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ - መ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ለሦስተኛ ጊዜ እና/ወይም ከዚህ በላይ የተፈፀመ ሲሆን ብር 20,000 /ሃያ ሺ/፣
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል ተራ ሀ እና ለ የተጠቀሱትን ድርጊቶች በተደራራቢነት ተፈጽሞ ሲገኝ ብር 20,000/ሃያ ሺ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ ማንኛውም ዲክላራሲዮን አቅራቢ እና/ወይም አጓጓዥ

በጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸሙ ላይ በቀጥታ ተጽዕኖ የሚያመጣ አደጋ ወይም ያልተጠበቀ ሁኔታ ሲከሰት በአካባቢው ባለ ጉምሩክ ጣቢያ ወይም አግባብ ላለው የመንግስት አካል በጽሁፍ ማሳወቅ ሲገባው ያላሳወቀ እንደሆነ

ሀ) ድርጊቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 5,000 /አምስት ሺ/፣

ለ) ድርጊቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ብር 10,000 /አስር ሺ/፣

ሐ) ድርጊቱ ለሦስተኛ ጊዜ እና/ወይም ከዚህ በላይ የተፈፀመ ሲሆን ብር 20,000 /ሃያ ሺ/ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) እና (3) የተዘረዘሩት ጥፋቶች ተደራርበው ሲገኙ ብር 20,000.00/ሀያ ሺህ/ ይቀጣል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

11. <u>ከቀረጥ ነፃ በገባ ዕቃ ያለአግባብ ስለመገልገል</u>

1/ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀፅ 163 /1/ መሠረት ከቀረጥ ነፃ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባን ዕቃ የአዋጁን ድንጋጌዎች በሚቃረን ሁኔታ፣

ሀ) የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ በሌላ አገልግሎት ላይ ያዋለ ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ እንደሆነ፣

ለ) ዕቃው ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ ሲሆን፣ በማናቸውም መልኩ ከቤተሰብ ውጪ በሌሎች ሰዎች አገልግሎት ወይም ይዞታ ሥር እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ) ዕቃው ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የገዛ፣ የተቀበለ፣ የተገለገለ፣ ያስተላለፈ፣ ወይም ለሌሎች ሰዎች አግልግሎት እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፣

ዕቃው በተያዘበት ጊዜ ወደ አገር እንደገባ ተቆጥሮ ለዕቃው ሲከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን 50% /ሀምሳ በመቶ/ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም ጥፋቱ ተፈጽሞ ሲገኝ ቀረጥና ታክሱን መክፈል ያለበት የቀረጥ ነጻ ባለመብቱ ወይም ዕቃ የተላፈለት ሰው ሲሆን በንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተገለጸውን ጥፋት የፈጸመው ሰው እና የቀረጥ ነጻ ባለመብቱ እያንዳንዳቸው ቅጣቱን እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ንብረቱን ይዞ የተገኘው ሰው የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ ከነቅጣቱ መክፈሉ ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ ይህንኑ የሚገልጽ ሰነድ ወይም ዲክላራሲዮን ሊሰጠው ይችላል፡፡

12. <u>በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባን ዕቃ ያለአግባብ ስለመገልገል</u>

የአዋጁ አንቀጽ 73(5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀፅ 164 መሠረት በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባን ዕቃ የአዋጁን ድንጋጌዎች በሚቃረን ሁኔታ ሲጠቀምበት የተገኘ እንደሆነ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቀረጥና ታክስ መጠን 50% በመቀጫ መልክ ከፍሎ ዕቃው ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

13. <u>ሌሎች ጥፋቶች</u>

1/ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 156-164 ከተመለከቱት ውጪ በአዋጁ ላይ የተመለከቱ ማናቸውንም ክልከላዎችን ወይም ግዴታዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ ካላከበረ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ/ ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተጠቀሱትን ክልከላዎች ወይም ግዴታዎች ለሁለተኛ ጊዜ ከፈጸመ ብር 7,000.00/ሰባት ሺህ/ ብር፣

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን ክልከላዎች ወይም ግዴታዎች ለሦስተኛ እና ከዚያ በላይ ፈጽሞ ከተገኘ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ/፣

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) እና (3) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ማንኛውም ሰው ክልከላዎችን ወይም ግዴታዎችን በተደራራቢነት ፈጽሞ ሲገኝ ብር 10000 /አስር ሺህ/ ይቀጣል፡፡

14. <u>ስለውሳኔ አሰጣጥ እና ውሳኔን ስለማሳወቅ</u>

1/ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የስራ ሂደት በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች እና ማስረጃዎች በቀረቡለት በ7 የስራ ቀናት ውስጥ በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ መስጠት አለበት፣

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ (6)፣(11) እና (12) የተመለከቱት ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ ቅጣቱን የሚወስነው የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት ይሆናል፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሕግ ማስከበር የስራ ሂደት የአስተዳደር ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት ከኢንተለጀንስ ወይም ከምርመራ ቡድን ወይም ከሌላ የሚመለከተው ክፍል ጥፋቱ መፈጸሙ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ማድረግ ይኖርበታል፣

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የህግ ማስከበር የስራ ሂደት ቅጣቱን ወስኖ ለአፈጻጸም ለጉምሩክ ስነ- ስርዓት የስራ ሂደት መላክ ይኖርበታል፣

5/ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጡ ማናቸውም ውሳኔዎች ጉዳዩ ለሚመለከተው ሰው በጽሑፍ መስጠት አለባቸው፣

6/ የቅጣት ማሳወቂያ ቅጽ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ መሠረት መሆን አለበት፣

7/ የተቀጣው ሰው በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በ15 ቀን ውስጥ ለዋና መ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ማቅረብ ይችላል ሆኖም ከህግ በተቀመጠው የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ካላቀረበ የቅጣት ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ዕቃዎችና ማጓጓዣዎችን ስለመያዝ፣ ስለማጣራት፣ ስለመውረስ እና ስለውሳኔ አሰጣጥ</u>

15. <u>የሚወረሱ ዕቃዎች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 147 በተደነገገው መሠረት የሚከተሉት ዕቃዎችና ማጓጓዣዎች የሚወረሱና ለመንግስት ገቢ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

1/ የሚወረሱ ዕቃዎችን ሲያጓጉዝ የተገኘ ማንኛውም ማጓጓዣ

ሀ) ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሰራ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል /ሻግ/ የተገጠመለት ከሆነ፣ ወይም

ለ) የማጓጓዥው ባለቤት እያወቀ የድርጊቱን መፈጸም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ወይም

ሐ) የማጓጓዣው ባለቤት ወይም ኃላፊ በአዋጁ አንቀጽ 143(4) መሰረት በማስታወቂያ ተጠርቶ ያልቀረበ እንደሆነ

2/ ሌሎች ዕቃዎች

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ማጓጓዣ ውርስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች የተገለፁት ዕቃዎች የሚወረሱ ይሆናል

ሀ) ማንኛውም የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት ወይም ሙከራ የተደረገበት ዕቃ፣

ለ) ማንኛውም የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበትና በማጭበርበር ተደብቆ የተገኘው ዕቃ ዋጋ በዲክለራሲዮን ከተገለፀው ዕቃ አጠቃላይ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከሃምሣ በመቶ /50%/ በላይ ሆኖ ከተገኘ ተደብቆ የተገኘው ዕቃ በሙሉ፣

ሐ) ክልከላ የተደረገበት ዕቃ ሆኖ :-

1. ወደ አገር ሲገባ ወይም ሲወጣ ወይም ሲተላለፍ የተገኘ፣
2. ወደ አገር ለመግባት ወይም ለመውጣት ወይም ሲተላለፍ በማጓጓዣ ላይ የተጫነ ወይም
3. በማንኛውም አለም አቀፍ መንገደኛ ወደ አገር ሲገባ ወይም ሲወጣ በማናቸውም መልኩ ይዞት የተገኘ ወይም፣
4. በማናቸውም መንገድ ወደ አገር ለማስገባት ወይም ለማስወጣት ሙከራ የተደረገበት ዕቃ በሙሉ፣

መ) ማንኛውም ገደብ የተደረገበት ዕቃ ሆኖ:-

1. የዚህ መመሪያ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ ሥልጣን ባለው አካል ወደ አገር እንዲገባ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ያልቀረበበትና ከአገር እንዲወጣ ተወስኖበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲወጣ ያልተደረገ ወይም፤
2. ሥልጣን ባለው አካል ከአገር እንዲወጣ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ያልቀረበበትና ፈቃዱ ከተከለከለበት ወይም ካልቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከጉምሩክ ቁጥጥር ያልወጣ ዕቃ፤

---

ሠ) በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያሉ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጭ በባለቤቱ እሽጋቸው ተከፈቶና ተለያይተው፣ ወደ ሌላ ሥፍራ ተዘዋውረው፣ ተለዋውጠው ወይም ተነካክተው የተገኙ ዕቃዎች፤

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

28/03/08

ረ) የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ ባለቤት ወይም ኃላፊ ያልታወቀ በሆነበትና ባለቤት ወይም ኃላፊ እንዲቀረብ በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎለት ማስታወቂያ በወጣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባለቤት/ኃላፊ ያልቀረበበት ፤

ሰ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16(1)ረ መሰረት መቃወሚያ ያልቀረበበት ዕቃ፤

የሚወረሱ ናቸው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የዕቃ ውርስ የዕቃውን መያዣ ወይም መጠቅለያ ይጨምራል።

4/ የሚወረስ ዕቃ ሆኖ እስከሚጣራ ድረስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(3) መሰረት ዋስትና ተይዞበት የቆየ ከሆነ እና በመመሪያው አንቀጽ 19(1) መሰረት ሲወሰን ዋስትናው ገቢ ይሆናል።

## 16. <u>ዕቃዎችና ማጓጓዣዎችን ስለመያዝ</u>

1/ ማንኛውም የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት በአዋጁ አንቀጽ 143 መሰረት የሚያዙ ዕቃዎችና ማጓጓዣዎችን በሚይዝበት ጊዜ፡-

ሀ) ዕቃውን ወይም ማጓጓዣውን የያዘ መሆኑን እና የተያዘውን ዕቃ አይነትና ብዛት እንዲሁም የማጓጓዣውን ዓይነትና ተፈጸመ የተባለውን የሕግ መተላለፍ ድርጊት ገልፆ ለዕቃው ባለቤት ወይም ለማጓጓዥው ባለቤት ወይም እቃውን በማጓጓዝ ላይ ላለው ሰው ዕቃውን እንደያዘ ወዲያውኑ ማረጋገጫ ሰነድ መስጠት ይኖርበታል፣ ሆኖም ዕቃው የተያዘው ከባለስልጣኑ የስራ ሰዓት ውጭ ሲሆን ማረጋገጫ መስጠቱ እስከ ተከታዩ የስራ ቀን ድረስ ሊራዘም ይችላል፣

ለ) የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ ባለቤት ወይም ኃላፊ የሆነ ሰው ያልታወቀ ከሆነ ይህ ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲቀርብ ቅ/ጽ/ቤቱ/ ማስታወቂያ ያወጣል፣

ሐ) ማስታወቂያው ባለዕቃው ወይም ባለማጓጓዣው የተጠራበትን ጉዳይና የሚቀርብበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክት ሆኖ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ጥሪ የተደረገለት ሰው ቀርቦ የማያስረዳ ከሆነ ዕቃው ወይም ማጓጓዣው የሚወረስ መሆኑን መግለጽ አለበት፣

መ) የሚወጣው ማስታወቂያ እንደአስፈላጊነቱ በጋዜጣ ወይም ዕቃው በተያዘበት አካባቢ በሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ ይኖርበታል፣

ሠ) ማስታወቂያው ስለተያዘው ማጓጓዣ የሚገልጽ ሆኖ የመኪናው መለያ/ዓይነት፣ ሰሌዳ ቁጥር፣ ሞተር ቁጥር፣ ሻንሲ ቁጥር እና ሌላም የተለየ መለያ ካለው የሄንኑ የሚገልጽ ማብራሪያ ማካተት አለበት።

ረ) የተያዘው ማጓጓዣ እና ዕቃ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተያዘ ለማስረዳት የሚያስችል የፎቶግራፍ የቪዲዮና መሰል ማስረጃዎችን መያዝና በአግባቡ መቀመጥ ይኖርበታል።

ሰ) በማስታወቂያ የተጠራው ሰው ወይም ዕቃው/መጓጓዣው የተያዘበትና ስመያዙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት ሰነዱ የደረሰው ሰው ሰነዱ በደረሰው ወይም ማስታወቂያው

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

... በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቃወሚያውን ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ማቅረብ ይችላል፣

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) መሠረት የውርስ መቃወሚያ የቀረበ ከሆነ የቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጁ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19(1) መሠረት ውሣኔ ይሰጣል፣

2/ ዕቃውን ወይም ማጓጓዣውን የሚያስወርሱ ህጋዊና ነባራዊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማጣራት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩን ወደ ምርመራ ቡድን በመላክ ምርመራ እንዲጣራ መደረግ ይኖርበታል፣

3/ የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ በአዋጁ አንቀጽ 147 መሰረት ያለምርመራ የሚወረስ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሲገኝ ያረጋገጠው የስራ ሂደት የውርስ ውሳኔ እንዲሰጥ ከመግለጫ ጋር ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ያቀርባል።

4/ በዋናው መ/ቤት በዚህ መመሪያ አንቀጽ (11) እና (12) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ዕቃዎችንና መሳሪያዎችን የያዘ እንደሆነ ለቀጣይ ስራ ዕቃው ሲገባ ድክላራስዮን ለተመዘገበበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ ከሆነ፣ የኮንትሮባንድ ዕቃ በተያዘበት አካባቢ ለሚገኘው ቅ/ጽ/ቤት የተያዘውን ዕቃ ከማብራሪያ ጋር ማስተላለፍ ይኖርበታል።

## 17. ስለማጣራት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ምርመራ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ በቅ/ጽ/ቤት ህግ ማስከበር ምክትል ስራ አስኪያጅ ይወሰናል፣

2/ በህግ ማስከበር የተላለፈው የምርመራ ትዕዛዝ ለምርመራ ቡድን በደረሰ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምርመራው ተጣርቶ መጠናቀቅ ይኖርበታል፣

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም ምርመራውን ለማጠናቀቅ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ የሚጠይቅ መሆኑን የምርመራ ቡድኑ የተረዳ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 145(1) እና (2) መሰረት የተያዘው ዕቃ በዋስትና የሚለቀቅ ዕቃ ከሆነ እንዲለቀቅ መግለጫ በማከል ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት ያቀርባል፤ የስራ ሂደቱም ለህግ ማስከበር ምክትል ስራ አስኪያጅ ያቀርባል፣

4/ የምርመራው ውጤት ዕቃውን ወይም ማጓጓዣውን ወይም ዋስትናውን በአዋጁ መሰረት የሚያስወርስ ስለመሆኑ የሕግ ማስከበር ምክትል ስራ አስኪያጅ የተረዳ እንደሆነ የውርስ ውሳኔ እንዲሰጥ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ ይኖርበታል፣

5/ የምርመራ ቡድኑ ምርመራን የሚያጣራው

ሀ) የማጓጓዣው ባለቤት በወንጀሉ ተሳትፎ ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ፣

ለ) የማጓጓዣው ባለቤት በማጓጓዣው ውስጥ የነበረና ያልነበረ መሆኑን ወይም መኪና ውስጥ ባልነበረበት ጊዜ ድርጊቱ እንዳይፈጸም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ያደረገው ጥረት ወይም የወሰደው እርምጃ ካለ ለማረጋገጥ፣

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተፈጸመው ወንጀል ተሳታፊ ወይም ተጠቃሚ መሆን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ፣

መ) ማጓጓዣው የዕቃ መደበቂያ ወይም ሻግ ያልተዘጋጀለት ወይም ያልተሰራለት መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሠ) በአዋጅ አንቀጽ 147 (1)(ሠ) መሰረት እሽጉ በማን እንደተከፈተ ለማጣራት፣

ረ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ (6) (11) እና (12) ላይ የተዘረዘሩት ጥፋቶች መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ፣

6/ የኮንትሮባንድ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ የምርመራ ቡድኑ የማጓጓዣው ባለቤት ወንጀሉ መፈጸሙን ያውቅ ነበር ብሎ ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማጣራት ይኖርበታል፡-

ሀ) ጭነቱ ባለቤቱ ከሚኖርበት ወደ ሌላ ቦታ የሚጓጓዝ ከሆነ ማጓጓዥያው ሙሉ ኮንትሮባንድ ጭነት ጭኖ ከሚኖርበት አካባቢ የተነሳ መሆኑን፣

ለ) የማጓጓዣው ባለቤት የመኪና ኪራይ ወይም ተጨባጭ ጥቅም የተቀበለ መሆኑን ወይም ለመቀበል የተስማማ መሆኑን፣

ሐ) የማጓጓዣው ባለቤት ከኮንትሮባንዲስቱ ጋር ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊትም ሆነ በኋላ በማንኛውም መልኩ ያደረጉት የነበረውን ግንኙነት መኖሩን፣

መ) የማጓጓዣው አሽከርካሪ ወንጀሉ ከመፈጸሙና ሲፈጸም ወይም ከተፈጸመ በኋላም ከባለቤቱ ጋር ያደረጉትን ማንኛውም ግንኙነትና ምክክር ወዘተ ማጣራት ይኖርበታል፡፡

ሠ) ማጓጓዣው ዕቃው ወደ ተጫነበት ቦታ ጭነት ሳይጭን የተጓዘ መሆኑንና ሙሉ ኮንትሮባንድ /የኮንትሮባንድ ጭነት ብቻ/ጭኖ የተመለሰ መሆኑን፣

ረ) የምርመራ ቡድኑ ከዚህ በላይ ባሉት ሁኔታዎች ብቻ ሳይወሰን ሌሎች ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ምርመራውን ሊያጣራ ይችላል፡፡

7/ ከምርመራ ውጤቱ ጋር በተያያዘ፡-

ሀ) የተፈጸመው ጥፋት በአስተዳደራዊ ጥፋቶች ውስጥ የሚካተት ሆኖ ሲገኝ የምርመራ ቡድኑ ጉዳዩን አስተዳደራዊ ቅጣቱ እንዲፈጸም ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት ከመግለጫ ጋር ማቅረብ አለበት፣

ለ) ጥፋቱ በአዋጁ ክፍል ሰባት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ የጉምሩክ ወንጀል ሆኖ ሲገኝ የምርመራ ቡድኑ የምርመራ መዝገብ አደራጅቶ ጉዳዩን ለዐቃቤ ህግ መላክ ይኖርበታል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

28/03/08

18. የዋስትና ዓይነት እና መጠን አወሳሰን

1/ የዋስትናው ዓይነት

ሀ) የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤት ከሆነ በመ/ቤቱ የበላይ አመራር በጹሁፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት፤

ለ) የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤት ካልሆነ የጥሬ ገንዘብ ወይም የባንክ ዋስትና በማስያዝ ይሆናል።

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ለ የተደነገገው ቢኖርም የተያዘው ዕቃ ተሽከርካሪ በሚሆንበት ጊዜ የኢንሹራንስ ዋስትና ለማስያዝ ይችላል።

መ) ዕቃው ወይም ማጓጓዣው በአዋጁ አንቀጽ 147 መሰረት የሚወረስ ከሆነ በዋስትና አይለቀቅም።

2/ የተከለከሉ፣ገደብ የተደረገባቸው ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ካልሆኑ በስተቀር የተያዙ ዕቃዎች ወይም ማጓጓዣዎች ምርመራቸው ወይም ጉዳያቸው ተጣርቶ ውሳኔ እስኪያገኙ ድረስ በዋስትና ሊለቀቁ ይችላሉ፤

3/ የሚያዘው የዋስትና መጠን የተያዘውን ዕቃ ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫው ወይም ከማጓጓዣው የገበያ ዋጋ መጠን ማነስ የለበትም፤

4/ ቅ/ጽ/ቤቱ የተያዙ ዕቃዎችን ወይም ተሽከርካሪዎች የዋስትና መጠን ለመወሰን የገበያ ዋጋ ጥናት በማድረግ ተመሳሳይ ዕቃዎች በገበያ ላይ ያላቸውን ወቅታዊ ዋጋ መሰረት ሊያደርግ ይችላል።

5/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል "የገበያ ዋጋ" ማለት ቀረጥና ታክስ ከፍለው ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች የሚሸጡበት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ነው፤

19. ስለመወሰን

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጾጽ 16(3) እና 17(4) መሰረት የውርስ ውሳኔ እንዲሰጥ የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት ስራ አስኪያጅ ውሳኔ በመስጠት ውሳኔው ለዕቃው ወይም ለማጓጓዣው ባለቤት በጹሁፍ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፤

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16(3) መሰረት ለስራ አስኪያጅ የቀረበው መግለጫና የውሳኔ ሀሳብ የሚያጠራጥር ሆኖ ሲያገኘው ሥራ አስኪያጁ ጉዳዩ በምርመራ እንዲጣራ ለምርመራ ቡድን ሊመራ ይችላል፤

3/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(3) መሰረት በዋስትና እንዲለቅ መግለጫ የቀረበለት የህግ ማስከበር ኃላፊ:-

ሀ) በዋስትና የሚለቀቀው ማጓጓዣ ሲሆን የማጓጓዣውን የገበያ ዋጋ ባለቤቱ እንዲያሲዝ በማድረግ ማጓጓዣውን በዋስትና እንዲለቀቅ ማድረግ ይችላል፤

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ለ) የተያዘው ሌላ ዕቃ ሲሆን የዕቃውን ጠቅላላ የገበያ ዋጋ በመወሰን በዋስትና እንዲለቀቅ ማድረግ ይቻላል፣

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የውርስ ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት የዕቃው ወይም የመጓጓዣው ባለቤት የመያዝ እርምጃ እንዲያውቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

20. <u>የውርስ ውሳኔ ይዘት</u>

ማንኛውም ዕቃ ወይም ማጓጓዣ በሚወረስበት ጊዜ የተፈጸመውን ጥፋትና የተጣሰውን ሕግ የሚጠቅስና ዕቃው ወይም ማጓጓዣው ውርስ መሆኑ ተገልፆ በቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ የተፈረመበት፣ የባለስልጣኑ ማህተም ያረፈበትና ለዕቃው ወይም ማጓጓዣው ባለቤት የተጻፈ ደብዳቤ ይሆናል፡፡

21. <u>በተደጋጋሚ ስለሚፈጸም ድርጊት</u>

1/ የኮንትሮባንድ ዕቃ በመጫን የሚያዙ ተሽከርካሪዎች እና ባለንብረቶችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ በቅ/ጽ/ቤቱ መያዝ ይኖርበታል፤

2/ በድጋሚ የሚያዙ ተሽከርካሪዎች ወይም ባለንብረቶች ባጋጠሙ ጊዜ ቀጣይ እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ባለቤቶች ተሣትፎ የላቸውም ተብለው የሚለቀቁ ተሽከርካሪ ባለቤቶች ንብረታቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል፤

3/ ከማስጠንቀቂያው በኃላ በድጋሚ ተሽከርካሪው የኮንትሮባንድ ወንጀል ተፈጽሞበት ከተገኘ ወይም አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ሰው ንብረት የሆነ ተሽከርካሪ ሆኖ ከተገኘ ባለንብረቱ እያወቀ ድርጊቱን ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን ጥረት እንዳላደረገ ተቆጥሮ ተሽከርካሪው የሚወረስ ይሆናል፡፡

4/ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሰረት ጥፋት ፈጽሞ ከተቀጣ ከ5 ዓመት በኋላ የሚፈጽመው ጥፋት እንደመጀመሪያ ጥፋት ይቆጠራል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

22. <u>ዕቃዎችን ይዞ ስለማቆየት</u>

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት የተጣለ መቀጫ ተፈጻሚ የሚደረገው መቀጫው እስኪከፈል ድረስ ጥፋት የተፈጸመበትን ዕቃ በመያዝ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተያዘው ዕቃ መቀጫውን ለማስፈጸም በቂ ካልሆነና የተያዘ ንብረት ከሌለ ባለስልጣኑ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የአስመጪውን /የተቀጪውን/ ንብረት በመያዝ ቅጣቱን ሊያስፈጽም ይችላል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

23. <u>መረጃ መያዝ</u>

1/ የቅ/ጽ/ቤቱ የሕግ ማስከበር ሥራ ሂደት እና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሥራ ሂደት በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ በመያዝ ለቅ/ጽ/ቤቱ፣ እና ድንበር አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ለታክስ ሕግ ተገዥነትና ሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በየወሩ ሪፓርት ያደርጋል፡፡

2/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም እንዲረዳ የታክስ ህግ ተገዢነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ባዘጋጀው የመረጃ ስርዓት መረጃውን መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

24. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ የተወሰነበት ሰው አስተዳደራዊ መቀጫ የውርስ ውሳኔ እና ይግባኝ ሲሆን ለባለስልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ስራ ክፍል ውሳኔው በደረሰው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

25. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1/ የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ ለመጨረስ ወጥቶ የነበረው መመሪያ ቁጥር 46/2002 እና ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ የወጣ መመሪያ ቁጥር 50/2003 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

2/ ትራንዚት ባለማክበር ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች በመመሪያ ቁጥር 16/2001 ከአንቀጽ 15 እስከ 17 እና መመሪያ ቁጥር 39/2002 ከአንቀጽ 2 እስከ 4 ድረስ የተቀመጡት ቅጣቶች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

3/ እንዲሁም አስቀድመው የነበሩ አሰራሮችና ልማዶች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

26. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ --------------- ቀን 2008 ዓ.ም

በከር ሻሌ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

# አባሪ

## የቅጣት ማሳወቂያ ቅጽ ቁጥር 1

ለ---------------------------------------------------------------

ጉዳዩ፡- በወጪና ገቢ ዕቃ ላይ የተጣለ ገደብን ባለማክበር የተጣለ ቅጣት ስለማሳወቅ፤

በዲክላራሲዮን ቁጥር ---------------------- አስመዝግበው ወደሀገር ውስጥ ያስገቡት/ከሀገር ለማስወጣት ያቀረቡት

1.
2.
3.

ዕቃ ከተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሲቀርብበት የሚገባውን ፈቃድ ያላቀረቡ ስለሆነ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ--- ፊደል ተራ ----መሰረት ብር -------------------/-----------/ተቀጥተው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃውን መልሰው ከሀገር እንዲያስወጡ/ወደ አገር ውስጥ እንዲመልሱ የተወሰነ መሆኑን እያስታወቅን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ዕቃው ወደመጣበት ሳይመለስ የቀረ እንደሆነ የሚወረስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ በዚሁ ውሳኔ ቅሬታ ከተሰማዎትም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 24 መሰረት ለቅ/ጽ/ቤቱ አቤቱታ አጣሪ ስራ ክፍል በ15 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

## የቅጣት ማሳወቂያ ቅጽ ቁጥር 2

ለ-------------------------------------------

ጉዳዩ፡- በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠ ቅጣት ስለማሳወቅ፤

በ-------------------------ቅ/ጽ/ቤት በዲ/ዮን ቁጥር ----------------ተመዝግቦ ለገባው ዕቃ በመመሪያ ቁጥር -------/2007 አንቀጽ------ንዑስ አንቀጽ------መሰረት ጥፋተኛ ሆነው ስለተገኙ ብር ………/ / የተቀጡ መሆኑን እያስታወቅን ይህ ውሳኔ እንዲደርስዎ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ቅጣቱን ከፍለው የተያዘብዎትን ዕቃ እንዲያወጡ እናሳስባለን፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ከተሰማዎትም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 24 መሰረት ለቅ/ጽ/ቤቱ አቤቱታ አጣሪ ስራ ክፍል በ15 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## <u>የውርስ ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ</u> ቁጥር 3

ለ---------------------------------------------

ጉዳዩ፡- <u>የውርስ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ስለማሳወቅ</u>፤

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 እና በመመሪያ ቁጥር --------/2007 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ -----ፊደል ተራ --------መሰረት ጥፋት ተፈጽሞ የተገኘ በመሆኑ

1.
2.
3.
4.

ውርስ እንዲደረግ የተወሰነ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ በጽሁፍ ለቢሮ ቅሬታ የማቅረብ መብት ያለዎት መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

## <u>የቅጣት ማሳወቂያ ቅጽ ቁጥር 4</u>

ለ ----------------------------------------------

ጉዳዩ፡- <u>በጊዜያዊነት ወደ አገር በገባ ዕቃ ያለአግባብ በመገልገልዎ የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ ስለማስታወቅ</u>፤

በ--------------------------ቅ/ጽ/ቤት በዲ/ዮን ቁጥር ----------------ተመዝግቦ በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባን ዕቃ የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌዎችን በሚቃረን ሁኔታ በ---------------ቀን ------------ዓ.ም ሲጠቀሙበት ስለተገኙ በዋስትና የተያዘው ብር --------------------/ /ለመንግስት ገቢ እንዲደረግና በመመሪያ ቁጥር ---------/2007 አንቀጽ 12(1) መሰረት ሊከፈል የሚገባውን የቀረጥና ታክስ መጠን ሃምሳ በመቶ ብር -----------------------/

/ መቀጫ እንዲከፍሉ እንዲሁም መቀጫውን በ15 ቀናት ውስጥ ከፍለው እቃውን ከሀገር እንዲያስወጡ የተወሰነ መሆኑን እያስታወቅን በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለዎት በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 24 መሰረት ለቅ/ጽ/ቤቱ አቤቱታ አጣሪ ስራ ክፍል በ15 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡